የቴዲ አፍሮ ታሪክ ተሠራ ዘፈን
ለቅንጅት መሪዎች ተለውጦ የተሰራ!

## ታሪክ ተሠራ

ሆ! ብሎ መርጦን በካርዱ (በድምጹ)
አሲዞ ሰንደቅ አለማ!
ሀዘን ነው መታሰራችን
አይበጅም ለኢትዮጵያ እማማ!

ብታሰር ቤተሰብ ጥዬ
ታስሬ ብናፍቃችሁ
ትልቁን እምነት በናንተ
ጥለናል እንግዲህ አይዟችሁ።

ከበደኝ ፓርላማ መግባት
ከበደኝ ህዝቤ ወገኔ
ከበደኝ በጄ ተጣራሁ
ከበደኝ በሁለት ታጤቴ።

በል ፍጠን ድሎ ናፍቆታል
በል ፍጠን ባንድነት ዛሬ
በል ፍጠን እንዳትታለል
በል ፍጠን በዘር ወገኔ።

(አልሆንለህ አለኝ እኔ
አልሆንለህ አለኝ
አንተን ጥሎ (ክዶ) መግባት ህዝቤ
አልሆንለህ አለኝ ) 2

አንበሳ (ቅንጅት የኛ)
አንበሳ ቅንጅት የኛ
አንበሳ ታሪክ ሰራ
አንበሳ የማይራሳ
አንበሳ ቅንጅት የኛ
አንበሳ የኢትዮጵያ
አንበሳ (2)

አዳራ ያቅሜን ሰራሁኝ
አዳራ እኔ ለሀገሬ
አደራ ትግሉን ሊያቆሙት
አዳራ (በግፍ) አሰሩኝ ዛሬ

ኢዮሃ! ከባንዲራው ነው
ኢዮሃ ካልኪዳናችን
ኢዮሃ አታፍሩም በኛ
ኢዮሃ መሪዎቻችን።

(አልሆንለህ አለኝ እኔ
አልሆንለህ አለኝ
አንተን ጥሎ (ክዶ) መግባት ህዝቤ
አልሆንለህ አለኝ) 1

አለልህ ቅንጅት ዛሬ
የነፃነት ተሰፋ
ይልቅ ባንድ ሆነህ
ቶሎ ባነዲራህን አንሳ።

(አልሆንለህ አለኝ እኔ
አልሆንለህ አለኝ
አንተን ጥሎ (ክዶ) መግባት ህዝቤ
አልሆንለህ አለኝ)

አለልህ ቅንጅት ዛሬ
ለአንዲት ኢትዮጵያ
አንተነህ ወጣቱ ያገር
ተተኪው አንበሳ።

አንበሳ ቅንጅት የኛ
አንበሳ ቅንጅት የኛ
አንበሳ ታሪክ ሰራ
አንበሳ የማይራሳ
አንበሳ ቅንጅት የኛ
አንበሳ የኢትዮጵያ
አንበሳ (2)

ኢዮሃ ጉሮ ወሸባ
ኢዮሃ ታሪክ ሰራቸሁ
ኢዮሃ ያገሬ ልጆች
ኢዮሃ ታውቁዋል ምርጫቹሁ

ኢዮሃ በል አንሳን ፎቶ
ኢዮሃ ታስረን በጅምላ
ኢዮሃ ብለህ ፃፍበት
ኢዮሃ ታሪክ ተሰራ!

እልል በል ያገሬ ጎበዝ
ለምዬ ወለታ
እስርቤት ገባሁኝ
ዛሬ ነፃነት ላመጣ።

በል ተነስ ያዝና በጅህ
የባንዲራ ዘንግ
በሰላም ትግልህን
ቀጥል እንዳትሸነፍ!

እልል በል ያገሬ ጎበዝ
ለምዬ ወለታ
ከእስርቤት ወጣሁኝ
ዛሬ ችግርዋንልፈታ

አንበሳ ቅንጅት የኛ
አንበሳ ቅንጅት የኛ

አንበሳ እዩት አርማውን
አንበሳ ግርማ ሞገሱን

አንበሳ እዩት ሲያኮራ
አንበሳ ቅንጅት የኛ!

አንበሳ ይቺ ባንዲራ
አንበሳ ናት እድለኛ
አንበሳ ዛሬም አኮራት
አንበሳ ቅንጅት የኛ!

ኢትዮጵያ የእኛ
ናት እድለኛ
አንበሳ
አንበሳ ቅንጅት የኛ

ዳንኤል ለገሰ
ከለንደን (ቅንጅት ዩኬ)

(ዜማ የቴዲ አፍሮ
ታሪክ ተሰራ)

Copyright© 2007